የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ ህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 3
ADDIS ABABA 17th November, 2005

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፫/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

ለአዘዞ-መተማ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት የተገኘው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ … ገጽ ፫ሺ፫፻፯

<u>**CONTENTS**</u>

**Proclamation No. 473/2005**

OPEC Fund for International Development Loan Agreement for Financing the Azezo-Metema Road Project Ratification Proclamation………. Page 3307

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፫/፲፱፻፺፰

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል <u>የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ</u>

ለአዘዞ-መተማ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፲፭ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /አሥራ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ የሚያስገኘው ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፲፪ ቀን ፪ሺ፬ በቬዬና የተፈረመ በመሆኑ፣፣

ይህንን የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለአዘዞ-መተማ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት የተገኘው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፫/፲፱፻፺፰ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 473/2005.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLLIC OF ETHIOPIA AND THE OPEC FUND FOR INTERNATIONAL DEVELOPMENT

**WHEREAS,** a Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development stipulating that the OPEC Fund for International Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of fifteen million United States Dollars (USD 15,000,000) for financing the Azezo-Metema Road Project, was signed in Vienna, on 12th day of May, 2004;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 13th day of October, 2005;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows;

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "OPEC Fund for International Development Loan Agreement for Financing the Azezo-Metema Road Project Ratification Proclamation No.473/2005."

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፲፪ ቀን ፪ሺ፬ በቪዬና የተፈረመው የብድር ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፭ሚሊዮን የአሜካን ዶላር /አሥራ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement signed between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development on the 12th day of May, 2004 is ratified;

## 3. power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of fifteen million United States Dollars (USD 15,000,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

The Proclamation shall enter into force on 17th day of November , 2005.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of November, 2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**